# የአስር ቀን የአየር ሁኔታ

# ግምገማና እና ትንበያ መጽሔት

## ከሜይ 11-20 የነበረው የአየር ሁኔታና ግምገማ እንዲሁም

## ከሜይ 21-31 የሚኖረው የአየር ሁኔታና ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ሜይ 2023

አዲስ አበባ

ርዕስ ገፅ


እ.ኤ.አ ከሜይ 11 እስከ 20/2023 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ........1
ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከሜይ 11 እስከ 20/2023 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ........3
ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከሜይ 11 እስከ 20/2023 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት........4
ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከሜይ 11 እስከ 20/20223 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን........5
ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር........5
እ.ኤ.አ ከሜይ 11 እስከ 20/2023 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርናው ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ........6
ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከሜይ 11 እስከ 20/2023 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ........6
እ.ኤ.አ ከሜይ 11 እስከ 20/2023 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ........7
ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከሜይ 11 እስከ 20/2023 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ........7
እ.ኤ.አ ከሜይ 21 እስከ 31/2023 የሚኖረው የአየር ሁኔታ........8
ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከሜይ 21-31, 2023 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ.........8
ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከሜይ 21-31, 2023 የሚኖረዉ ከባድ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ.........8
ካርታ 8 እ.ኤ.አ. ከሜይ 21-31, 2023 የሚኖረዉ የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን........8
እ.ኤ.አ ከሜይ 21 እስከ 31/2023 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ........9
እ.ኤ.አ ከሜይ 21 እስከ 31/2023 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ........10

## እ.ኤ.አ ከሜይ 11 እስከ 20/2023 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ


በሜይ የሁለተኛ አስር ቀናት የበልግ ዝናብ ሰጪ የአየር ሁኔታ ገጽታዎች አንፃራዊ በሆነ መልኩ በምዕራብና በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ተጠናክሮ ተስተውሏ፡፡ በተጨማሪም የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በመጠንም ሆነ በስርጭት ረገድ አነስተኛ የዝናብ ስርጭት ነበራቸው፡፡ በዚህም መሠረት በአስሩ ቀናት ውስጥ በአብዛኛው የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው የተስፋፋ ዝናብ ያገኙ ሲሆን፤ በአንዳንድ ቦታዎቻቸው ላይ ደግሞ ከ30 ሚ.ሜ በላይ ከባድ ዝናብ ነበራቸው፡፡ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች መካከል በሚ.ሜ በጎሬ 38.0፣ በጅማ 39.0፣ በአዲስ አበባ 30.2፣ በሀሮማያ 75.0፣ በአርጆ 34.4፣ በጭራ 57.3፣ በደብረ ታቦር 37.0፣ በዲላ 30.5፣ በደምቢ ዶሎ 32.2፣ በወሊሶ 49.2፣ በማሻ 36.4፣ 70.6፣ በሞጣ 36.3፣ ቢ,በሲርንቃ 36.0፣ በግዳ አያና 40.5በሊሙ ገነት 37.2፣ በመካነ ሰላም 35.0፣ በሜኤሶ 48.7በተርጫ 38.3 እንዲሁም በጭፍራ 46.5 በሚ.ሜ ይገኙበታል፡፡

በሌላ በኩል የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን በሀገሪቱ ቆላማ አካባቢዎች ላይ ማለትም በምዕራብ እና በደቡብ ምዕራብ፣ በሰሜን ምስራቅ፣ በደቡብ ምሥራቅ እና በደቡብ የሀገሪቱ ዳርቻዎች ላይ በአብዛኛዎቹ ቀናት ላይ ከ35 ዲ.ሴ በላይ ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ ከ35 ዲ.ሴ በላይ የተመዘገበባቸውን ሥፍራዎች ለመጥቀስም ያህል ድሬደዋ 35.0፣35.6፣36.0 በጭፈራ 35.0፣36.5፣37.5፣38.0፣38.5፣39.0፣ በፉኚዶ 36.0፣36.5፣37.0፣በኑራ ኤራ 35.2፣36.036.2፣በፓዌ36.0፣37.4፣37.6፣37.8፣በሽርኮሌ35.0፣36.0፣36.2፣37.1፣38.1፣39.0፣በሳዉላ36.6፣በፅፅቃ35.0፣37.8፣38.6፣38.8፣39.2፣39.4፣በመተሃራ35.5፣36.0፣37.8፣38.0፣በዳሊፋጊ37.0፣38.0፣ በጋምቤላ 35.5፣35.8፣37.2፣38.0 ዲ.ሴ ሲሆን፤


በተጨማሪም በጥቂት አከባቢዎች ላይ ደግሞ ከ40 ዲ.ሴ በላይ ተመዝግቧል፡፡ ለአብነትም በአዋሽ አርባ 40.0፣40.5፣41.0፣በዱብቲ 42.0፣42.5፣43.0፣44.0በመተማ 41.0፣41.6፣41.8፣42.0፣42.6፣ በሰመራ 40.0፣40.4፣40.6፣40.8፣41.4፣41.8፣42.0፣በጎዴ41.0፣41.2፣፣41.4፣41.8፣በሚሌ40.0፣40.5፣41.0፣42.5 ዲ.ሴ የደረሰ የቀኑ ከፍተኛ የአየር ሙቀት መጠን እንደተመዘገበ ከየጣቢያዎቹ የተሰበሰቡ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም፤ከኦሮምያ ክልል በምዕራብ ወለጋ፣ቦረና፣ጉጂ፣ሊበን ዞኖች በስተቀር ሁሉም ዞኖች፣ከአማራ ክልል በደቡብ ጎንደር፣ሰሜን እና ደቡብ ወሎ፣ምስራቅ ጎጃም፣የኦሮምያ ልዩ ዞን፣ ሰሜን ሸዋ፣ ከጋምቤላ ክልል ኑዌር፣አኙዋክ እና ማዠንግ ዞኖች፣ከሱማሌ ክልል ፋፋን እና ሲቲ ዞኖች፣ ሁሉም የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦች እና ህዝቦች ክልል ዞኖች፣ከአፋር ዞን 1 እና 4፣ አዲስ አበባ፣ ድሬ ዳዋ እና ሀረሪ  ላይ ከ12-135 ሚ.ሜ የሚደርስ ከ1-10 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2) ፡፡


ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር ከአማራ ክልል በሰሜን እና ደቡብ ወሎ ፣ ደቡብ ጎንደር፣ የኦሮምያ ልዩ ዞን፣ ሰሜን ሸዋ፣ ከኦሮምያ ክልል ምዕራብ ወለጋ፣ሆሮ ጉዱሩ፣ደቡብ ምዕራብ ሸዋ፣ምስራቅ ሸዋ፣ምስራቅ እና ምዕራብ ሃረርጌ፣ኢሉአባቦር፣ቄለም ወለጋ፣ከአፋር ዞን 4፣ከሱማሌ ክልል ሲቲ ዞን፣ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሸካ፣ከፋ፣ኮንታ እና ዳዉሮ ዞን፣ከደቡብ ብሄር ብሄረ ሰቦች እና ህዝቦች ክልል ጎፋ፣ሀድያ፣አላባ፣ከንባታ፣ለሲዳማ ክልል ጌድዎ አዲስ አበባ፣ ድሬ ዳዋ እና ሀረሪ ላይ መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ የተመዘገበ ሲሆን፤ የተቀሩት የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከመደበኛ በታች የሆነ የዝናብ መጠን ተመዝግቧል(ካርታ 3)፡፡




ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከሜይ 11 እስከ 20/2023 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ





ካርታ 2   እ.ኤ.አ ከሜይ 11 እስከ 20/2023 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት




ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከሜይ 11 እስከ 20/20223 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር

## እ.ኤ.አ ከሜይ 11 እስከ 20/2023 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርናው ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ


ባሳለፍነው ሁለተኛዉ የሜይ አስር ቀናት የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑ የሀገሪቱ አካባቢዎች በመጠንም ሆነ በስርጭት ረገድ አነስተኛ የዝናብ ስርጭት የነበራቸው ሲሆን በአስሩ ቀናት ውስጥ በአብዛኛው የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው የተስፋፋ ዝናብ አግኝተዋል፡፡ ይህም ሁኔታ የበልግ አብቃይና የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ ቦታዎችን ያካተተ እርጥበት ዘግይተውም ሆነ ቀደም ብለው ለተዘሩት የበልግ ሰብሎች ቀጣይ እድገት ጠቀሜታ ነበረው፡፡ በተለይም የእርጥበቱ ሁኔታ ወደ ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች የተስፋፋ ሲሆንና ይህም ሁኔታ ለረጅም ጊዜ ሰብሎች የማሳ ዝግጅትና ለዘር ስራ እንቅስቃሴ ለቋሚ ሰብሎች የውሀ ፍላጎት መሟላትና በአርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች አካባቢዎች አመቺ ሁኔታን የፈጠረ ነበር፡፡ በተጨማሪም በአንዳንድ ቦታዎች ላይ አልፎ አልፎ የነበረው ከባድ ዝናብ ምንም እንኳን በጥቂት ቦታዎች ላይ አሉታዊ ጎን ቢኖረውም ለአብዛኛው የእርሻ እንቅስቃሴ ጠቀሜታው የጎላ ነበር ፡፡ በሌላ በኩል በሀገሪቱ ቆላማ አካባቢዎች የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን በተለይም በምዕራብ እና በደቡብ ምዕራብ፣ በሰሜን ምስራቅ፣ በደቡብ ምሥራቅ እና በደቡብ የሀገሪቱ ዳርቻዎች ላይ በአብዛኛዎቹ ቀናት ከ35 ዲ.ሴ በላይ በተጨማሪም በጥቂት አከባቢዎች ላይ ደግሞ ከ40 ዲ.ሴ በላይ ሆኖ የተመዘገበ ሲሆን ይህም የነበረው ፀሐያማና ሞቃታማ የአየር ሁኔታ ከእፅዋትና ከአካባቢያቸው የሚኖረውን ትነት ስለሚያባብሰው ከበልግ ዝናብ መውጣት ጋር ተዳምሮ በወቅቱ አጠቃላይ የግብርና ሥራ እንቅስቃሴ እንዲሁም በአርብቶ አደሩ አካባቢ የእንስሳት መኖና ውኃ አቅርቦት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ነበረዉ፡፡




ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከሜይ 11 እስከ 20/2023 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

## እ.ኤ.አ ከሜይ 11 እስከ 20/2023 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው ሜይ ሁለተኛ አስር ቀን በመካከለኛው እና የደቡብ ምዕራብ ተፋሰሶች ላይ የተሻለ ዕርጥበት ነበራቸው፡፡ በተለይምየመካከለኛውና የላይኛው ኦሞ ጊቤ፣ አባይ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ የላይኛው ገናሌዳዋ፣ ባሮ አኮቦ፣ አዋሽ እና በጥቂት ተከዜ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እርጥበት እስከ ከፍተኛ እርጥበት የተስተዋለባቸው ናቸው፡፡አብዛኛው ዋቤ ሸበሌ፣ ገናሌ ዳዋ፣ ኦጋዴን እና አፋር ደናክል ተፋሰሶች ላይ ደረቅ እና ከፊል ደረቅ ሁኔታ ነበራቸው፡፡




ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከሜይ 11 እስከ 20/2023 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

## እ.ኤ.አ ከሜይ 21 እስከ 31/2023 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በመደበኛ ሁኔታ የሜይ የመጨረሻዎቹ አሥራ አንድ ቀናት የበልግ ወቅት መጨረሻዎቹ ቀናት ሲሆኑ የእርጥበቱም ስርጭት የመኸር ወቅት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት የምእራባዊ አካባቢዎች ላይ ይበልጥ መስፋፋት ይጀምራል፡፡

በሚቀጥለው የሜይ የመጨረሻዎቹ አሥራ አንድ ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ከክረምት ወቅት መጀመር ጋር በተያያዘ በምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ በመጠንም ሆነ በሥርጭት የተጠናከረ ዝናብ የሚኖር ሲሆን እርጥበታማው የአየር ሁኔታ ከቀን ወደ ቀን በተለይም በምዕራብና በሰሜን ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ የእርጥበት ሁኔታ ሊኖር እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ይህም ሁኔታ በተለያየ የዕድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙት የበልግ ሰብሎች ጠቀሜታ ሲኖረው ለቋሚ ተክሎች የውሀ ፍላጎት መሟላት እንዲሁም ለአርብቶ አደሮች እና ከፊል አርብቶ አደሮች ለግጦሽ እና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት የጎላ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ በተጨማሪም በምዕራብ አጋማሽ የሀሪቱ አካባቢዎች ላይ እየተስፋፋ እንደሚሄድና በመጠንም ሆነ በሥርጭት የተጠናከረ እንደሚሆን የሚጠበቀው እርጥበት ቀደም ብለው የመኸር እርሻ እንቅስቃሴን ለጀመሩት አካባቢዎች የሚገኘው እርጥበት የጎላ ጠቀሜታ እንደሚኖረው እና በተለይም የረጅም ጊዜ ሰብሎችን ለመዝራትና አስፈላጊ ዝግጅት ለማድረግ መልካም አጋጣሚ እንደሚፈጥር ይጠበቃል፡፡ በሌላ መልኩ በአንዳንድ ጥቂት ሥፍራዎች ከከባድ ዝናብ ሊኖራቸው ስለሚችል ቅፅበታዊ ጎርፍን ከመከላከል ጎን ለጎን የውኃ ማቀብ ተግባራትን ለማከናወን የሚያስችል ስለሚሆን፤ የሚመለከታቸው አካላት ቅድመ ዝግጅት እንዲያደርጉ ይመከራሉ፡፡

## እ.ኤ.አ ከሜይ 21 እስከ 31/2023 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በውሃዉ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት የሜይ አስራ አንድ ቀናት በምዕራብ፣ በሰሜን ምዕራብ እና ደቡብ ምዕራብ በሚገኙ ተፋሰሶች ላይ የተሻለ የእርጥበት ሁኔታ እንደሚኖራችው ይጠበቃል፡፡ በዚህም መሰረት አብዛኛው አባይ፣ ባሮአኮቦ፣ ተከዜ፣ ኦሞ ጊቤ፣ የላይኛው እና የመካከለኛው ስምጥሸለቆ፣ አዋሽ፣ የላይኛው ገናሌ ዳዋ እና ዋቤ ሸበሌ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እርጥበት እስከ ከፍተኛ እርጥበት እንደሚያገኙ ይጠበቃል፡፡ከዚሁ በተያያዘ ሊኖር በሚችለው ከፋተኛ እርጥበት ለጎርፍ ተጠቂ በሆኑ ቦታዎቻቸው ላይ በህይወት እና በንብረት ላይ ጉዳት እንዳይደርስ የሚመለከተው አካል ትብብር እና ቅድመ ዝግጅት እንዲደረግ እንመክራለን፡፡የተቀሩት ሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ ደረቅ እና ከፊል ደረቅ ሁነው እንደሚቆዩ ይጠበቃል፡፡